# ሰምተዋል?

## እስከ $4,824 ወይም ከዛ በላይ ልያገኙ ይችላሉ።

**የሚገባዎትን ጥቅም ለማግኘት የአገር ውስጥ ገቢ ታክስን ለመገመት የሚያስችለውን ፎርም ሞልተው ይላኩ።**

- በ2008 ሰርተው ከሆነ፤ ከርሶ ጋር የሚኖሩ ልጆች ካለዎትና የዓመት ገቢዎ ከ $39,000 በታች ከሆነ።

**ወይም**

- ከርስዎ ጋር የሚኖሩ ልጆች ባይኖሩም የዓመት ገቢዎ ከ $13,000 በታች ከሆነ፤

**የገቢ ታክስ እየተቆረጠብዎ ካልነበረም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የሚሰጥና በቤተሰቡ ያሉ ጥገኞች ብዛት መሰረት አድርጎ የሚሰጥ ገንዘብ ለማግኘት፤**

**ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ ፤** የታክስ እርዳታ **በነፃ** ሊያገኙ ይችላሉ።
ለበለጠ የአገር ውስጥ ገቢን በ 1-800-829-1040 ያነጋግሩ።

ለተጨማሪ መረጃ

______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________

TAX CREDITS FOR PEOPLE WHO WORK
EIC AND CHILD TAX CREDIT

## ከደሞዝ/ከሥራ ገቢ የተነሳ የሚታሰብ የታክስ አበል ወይም/ክሬዲት እና የልጅ ታክስ ቅናሽ/ክሬዲት የታክስ ክፍያዎትን ሊያስቀንሱ እና ከአገር ውስጥ ገቢ ተመላሽ ጥሬ ገንዘብ ሊያገኙ ይችሉ ይሆናል!

- እ ኤ አ በ2008 ከስድስት ወራት ያላነሰ ጊዜ ሥራ ሠርተው ከሆነ (ለአበሉ/ቅናሹ/ክሬዲቱ) ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።
- መክፈል የሚገባዎት የገቢ ታክስ ባይኖርም እንኳ (አበሉን/ቅናሹን/ክሬዲቱን) ሊያገኙ ይችላሉ።

## በ2008 ከግማሽ ዓመት በላይ ከርስዎ ጋር የኖሩ ልጆች ከነበሩ፡

- **ከደሞዝ/ከሥራ ገቢ የተነሳ የሚታሰብ ታክስ አበል/ክሬዲትን በተመለከተ፡ ልጆች በ2008 ዕድሜያቸው ከ19 ዓመት በታች መሆን ይኖርበታል (የሙሉ ጊዜ ተማሪዎች ከ24 ዓመት በታች ሊሆኑ ይችላሉ፡ አካለ ስንኩላን የሆኑ ልጆች የዕድሜ ገደብ የለባቸውም።)**
- **በልጆች ምክንያት የሚሰጥ ታክስ ቅናሽ/ክሬዲትን በተመለከተ፡ ልጆች በ2008 ዕድሜያቸው ከ17 ዓመት በታች መሆን ይኖርበታል።**

## ከርስዎ ጋር የኖሩ ልጆች ባይኖሩ፡

- ዕድሜዎ በ2008 በ25 ዓመትና በ64 ዓመት መካከል ከሆነ ከደመወዝ/ከሥራ ገቢ የተነሳ ለሚሰጥ ታክስ አበል/ክሬዲት ሊያመለክቱ ወይም ሊጠይቁ ይችላሉ።

## ደመወዜ/ከሥራ የማገኘው ገቢ ስንት መሆን አለበት? የማገኘው የታክስ አበል ወይም ቅናሽ (ክሬዲት) ምን ያህል ነው?

| ለደመወዝ/ሥራ ገቢ አበል (ክሬዲት)፡ ለ – | የደመወዝ/የሥራ ገቢ ከሚከተለው በታች ከሆነ | እስከሚከተለው የደመወዝ/የሥራ ገቢ አበል ያመልክቱ |
|---|---|---|
| 1 ልጅ | $33,995 | $2,917 |
| 2 ወይም ከሁለት በላይ ልጆች | $38,646 | $4,824 |
| ልጆች ከሌልዎት | $12,880 | $438 |
| **ለልጆች ታክስ ቅናሽ/ክሬዲት** | **ገቢዎ ከሚከተለው በላይ ከሆነ** | **እስከሚከተለው የልጅ ታክስ አበል/ክሬዲት ያመልክቱ** |
| 1 ወይም ከአንድ በላይ ልጆች | $8,500 | $1,000 |

***ለባለትዳር ሰራተኞች የገቢ ክሬዲት የገደብ መጠን በ$3,000 ከፍ ያለ ነው።***

## የዩናይትድ ስቴትስ (አሜሪካ) ዜጋ ባልሆንስ? የሚሠሩና ሌሎች መመሪያዎችን የሚያሟሉ ስደተኞች (Immigrants) ታክስ ፎርም ለመሙላት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

- **ከደመወዝ/ከሥራ ገቢ የተነሳ የሚታሰብ ታክስ አበል/ክሬዲትን በተመለከተ፡** ሠራተኛ፡ ባለቤትና ማንኛውም/ቀም የሚመለከተው/ታት ልጅ ሕጋዊ የሆነ የሶሻል ሰኪዩሪቲ ቁጥር ያስፈልገዋል/ጋታል።
- **በልጆች ምክንያት የሚሰጥ ታክስ ቅናሽ/ክሬዲትን በተመለከተ፡** የሶሻል ሰኪዩሪቲ ቁጥር (SSN) ወይም ግላዊ የታክስ ከፋይ መታወቂያ ቁጥር (ITIN) ይፈለጋል።

## የደመወዝ/የሥራ ገቢ አበል/ክሬዲት እና የልጅ ታክስ ቅናሽ/ክሬዲት ለማግኘት የፌደራል ታክስ ፎርም ሞልተው ይመልሱ፡ ታክስ ፎርም ለመሙላት ነጻ እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ!!!

- ቪታ (VITA)፡ በፈቃደኛነት/በነፃ የገቢ ታክስ ሥራ እርዳታ (Volunteer Income Tax Assistance) – ለሰዎች ታክሳቸውን በመሥራት እርዳታ ይሰጣል።
- ቪታ በዚህ በታክስ ሥራ በሠለጠኑ የማኅበረተሰቡ ቡድኖች ይካሄዳል። በአካባቢዎ የሚገኝ የቪታ ቢሮን ለማወቅ 1-800-829-1040 ደውለው ይጠይቁ።

## የሚሠሩ ከሆነ፡ ሌሎች መንግሥታዊ/ህዝባዊ ጥቅሞችን ሳያጡ እነዚህን የታክስ አበሎች (ክሬዲቶች) ማግኘት ይችላሉ

እንደ ምግብ ደረሰኝ (ፉድ ስታምፕ)፡ የሶሻል ሰኩዩሪቲ ገቢ፡ የጤና-እርዳታ (ሜዲክኤድ)፡ የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ፡ ወይም የመንግሥት ቤት፡ የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ለማግኘት ወይም ለማሳደስ ሲያመለክቱ በሚደረገው ማጣሪያ ከ(አገር ውስጥ ገቢ) የሚመለሱልዎ የደመወዝ/ከሥራ ገቢ አበሎች/ክሬዲት እንደ ገቢ አይታሰብቦትም። አንዳንድ የጥቅም ፕሮግራሞች ከአገር ውስጥ ገቢ የሚመለስልዎትን ገንዘብ ለምን ያህል ጊዜ በባንክ ሂሳብ ለማቆየት እንደሚችሉ የጊዜ ገደብ ሊኖራቸው ይችላል።

## ከሚመለስልዎት የታክስ አበል/ክሬዲት የተወሰነን መጠን በየጊዜው ከደሞዝዎ ጋር አስቀድመው ሊያገኙ ይችላሉ

አንዳንድ ሠራተኞች የደሞዝ/የሥራ ገቢ አበል/ክሬዲት ክፍያን ከፊሉን አስቀድመው ከደመወዛቸው ጋር፡ እና የቀረውን ደግሞ ታክሳቸውን ሞልተው ሲመልሱ ከአገር ውስጥ ገቢ በቼክ ማግኘት ይችላሉ። የአገር ውስጥ ገቢን ፎርም W-5 (IRS Form W-5) ከአሠሪዎ ወይም ከአገር ውስጥ ገቢ በስልክ 1-800-829-3676 ወይም በድኅረ-ገጽ *www.irs.gov* ማግኘት ይችላሉ።